# የስኬት ሰገነት



*ኢትዮጵያን በዓለምዐቀፍ መድረኮች ላይ በመልካም ከሚያስጠሩ ሰዎች አንዷ ናቸው - ዶ/ር ሰገነት ቀለሙ። **መብራቱ በሳቸው** ከፍኖተሠላም የፈለቁትን ዶ/ር ሰገነት ቀለሙን የስኬት ሕይወት ተሞክሮ ከሳይንቲስቷ አንደበት እና ሌሎችም ምንጮች አጠናክሮ ባቀረበው መጣጥፍ ያስነብበናል። መብራቱ፣ የሳይንቲስቷ ሕይወት ለአንባቢ ልብ ይበልጥ እንዲቀርብ ‹አንቺ› እያለ መተረክ መርጧል።*



ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ወጎች ጠንከር በሚሉበት ማኅበረሰብ ለሴቶች የሚሰጠው ቦታ ከወንዶች በብዙ ይለያል፤ ፈተናውም ብዙ ነው። ያለዕድሜ ጋብቻን፣ የሥራ ጫናን፣ ለወንዶች የተከለለን አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን መጋፈጥ፣ መቋቋምና ማለፍ ይጠይቃል - ትምህርት ቤት ገብቶ ለታላቅ ደረጃ ለመድረስ። በገጠራማዋ የፍኖተሠላም ከተማ ተወልዳ ላደገችው ዶ/ር ሰገነት እነዚህን ሁሉ ተቋቁሞ ማለፍ ትልቅ ፈተና ነበር። እንደ ብዙዎቹ የአገራችን አካባቢዎች እንጨት መልቀም፣ ወንዝ ወርዶ ውኃ መቅዳት፣ ገበያ መውጣት፣ በእርሻ ሥራ መሠማራትና በቤት ውስጥ ሥራዎች መጠመድ በተለይ ለሴቶች የዘወትር ተግባር እንደመሆኑ ዶ/ር ሰገነትም በነዚህ ሁሉ ተሳትፋለች፣ አልፋለች። ዶ/ር ሰገነት ከሌሎች የሴት ጓደኞቿ ለየት የሚያደርጋት ከአካባቢው ባሕል ወጣ ባለ መልኩ ወንዶች የሚውሉበት እንደ ዛፍ መውጣት፣ አህያ መጋለብና የመሳሰሉ ቦታዎች ትውል እንደነበር ትናገራለች። ይሄ ድርጊቷ ከሌሎች ሴት ጓደኞቿ በተለየ ነጻነትን ለመጎናጸፍ እንዳስቻላት ትናገራለች።

በልጅነቷ ነጻነቷን አስጠብቃ ስለነበር ምንም እንኳን በሴቶች ላይ የተጫነውን የሥራ ጫና መሸከም ቢኖርባትም እንደሌሎቹ ሴት ጓደኞቿ በልጅነቷ ከመዳር ለመዳን ችላለች። በትምህርቷ የመቀጠል ዕድልንም አግኝታለች። ይሄን ዕድሏን ተጠቅማ በጣም ጥብቅ የነበረውን የትምህርት አሰጣጥና የሥራ ጫና ተቋቁማ ለከፍተኛ ማዕረግ ለመብቃት ብብዙ ትታትር ነበር። በእነዚህ ሁሉ ውጣ ውረዶች አልፋ ነበር የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በከፍተኛ ውጤት ያጠናቀቀችው።

አስተዳደጓ በሃይማኖት የታነፀ፣ የሥራ ባሕሉ ጥብቅ የሆነ ማኅበረሰብ በመሆኑ የጠበቀ የሥራ ባሕልና ታታሪነት እንዳስተማራት ትናገራለች። አንዳንዴ ከዚህ የማኅበረሰቡ እሳቤ ወጣ የማለት ዝንባሌ እንደነበራት የምትናገረው ዶ/ር ሰገነት አንዳንዴ የማይጠየቁ የሚባሉ ጥያቄዎችን የአካባቢውን ቄሶች ትጠይቅ እንደነበርና እናቷ ይገስጽዋት እንደነበር ታስታውሳለች። ትምህርት አሰጣጡም ጠንከር ያለ ቅጣት የነበረውና ጥብቅ ነበር። "መምህር ኃይለሥላሴ የተባሉትን የአንደኛ ደረጃ አስተማሪዬን አልረሳቸውም" የምትለው ዶ/ር ሰገነት፣ "ጥፋት የተገኘበት ተማሪ የሚቀጣው ቅጣት እጅግ ከባድ እንደነበር" ትናገራለች። በዚህ ሁሉ አልፋ አስተዳደጓ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ያበረከተላትን አስተዋፅዖ ስትናገር፦ "አስተዳደጌ የሰጠኝ ትልቅ ቁምነገር ቢኖር ጥልቅ የሥራ ባሕል፣ ዲሲፕሊን፣ ጊዜን ባግባቡ መጠቀም እና የቤተሰብ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ መረዳት ነው፤" ትላለች።

## ከፍተኛ ትምህርትና የሕይወት ፈተናው

በጠንካራ መሠረትና የሥራ ባሕል ባንድ በኩል የሥራና የባሕል ጫና፣ በሌላ በኩል ያሳለፈችው ዶ/ር ሰገነት በወቅቱ ለማለፍ ከባድ የነበረውን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን በከፍተኛ ውጤት በማምጣትና ለሴቶች የማይደፈር የሚመስለውን ጉዞ ወደ አለማያ (በአሁኑ አጠራር ሀሮማያ) ▶

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሆነ፡፡ ከፍኖተሠላም ደብረማርቆስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከደብረማርቆስ ሀሮማያ እርሻ ኮሌጅ፣ ብዙ ፈተናና ጫናን ተቋቁማ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በዕፀዋት ሳይንስ የከፍተኛ ማዕረግ የተቀበለች ሲሆን፣ በወቅቱ ከአካባቢዋ የመጀመሪያዋ ሴት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበረች፡፡ ሁለት መቶ ከሚሆኑት የክፍሏ ተማሪዎች ብቸኛ ሴት ብትሆንም በከፍተኛ ማዕረግ ነበር ያጠናቀቀችው፡፡ሁለተኛና የዶክትሬት ዲግሪዋን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና አሜሪካን አገር እንዲሁም በኮርኔል ዩኒቨርሲቲ የ‹ፖስት-ዶክተራል ፌሎው› አግኝታለች፡፡

“ሕይወት ሁል ጊዜም አልጋ ባልጋ አይደለም፤ በተለይም ለሴት ልጅ” የምትለው ዶ/ር ሰገነት ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ በተለያዩ ዓለምዐቀፍ የምርምር ተቋማት ውስጥ ሠርታለች፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ብዙ ተግዳሮቶች እንደገጠሟት የምትናገረው ዶ/ር በተለይ አሜሪካን አገር የሁለተኛ ዲግሪዋን ስትሠራ የገጠማትን ታስታውሳለች፡፡ “ማስተርስ ዲግሪዬን አሜሪካ አገር ሞንታና ስቴት በምሠራበት ወቅት ከአንዲት መልካም ከሆነች ሚክሲኳዊት’ጋ እና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን የ‹ስኮላርሽፕ› ገንዘባችን በቂ ስላልነበር ተጨማሪ ሥራዎች መሥራት ነበረብን፡፡ ተቀጥሮ ለመሥራት ግን የውጭ አገር ዜጋ ተማሪዎች ስለነበርንና የሥራ ፈቃድ ስላልነበረን ተቀጥረን መሥራት አንችልም ነበር፡፡ በመሆም በአካባቢው የገበሬዎች እርሻ ስለነበር ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት የወዳደቀ ምርት መልቀምና ለገበያ ማቅረብ፣ ሰዎች የጣሏቸውን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች በመለቃቀም ለጋራዥ መሸጥ፣ ዘናጭ የሆኑ የሞንታና ኗሪዎች የሚሰጡንን የቀዘቀዘ ስጋ በመጠቀም ገንዘብ እናገኝ ነበር” ትላለች፡፡

ሁለተኛው ተግዳሮቷ በቆዳ ቀለምና በፆታ የሚመጣ መገለልና አድሎ ነው፡፡ በዓለም ላይ በብዙ ቦታዎች በቆዳ ቀለምና በጾታ የሚመጣ መገለልና አድሎ አለ የምትለው ዶ/ር “ሰዎች እንዴት ይሄን የመሰለውን አድሎና መገለል ተቋቁመሽ አለፍሽው ይሉኛል፡፡ እኔ ግን በጠንካራ ሥራና ስብዕና ለጥቂት ሒሊና ቢሶች ቦታ ባለመስጠት በየትኛውም ቀለምና ፆታ ውስጥ ብንሆን ለውጤት መብቃት እንችላለን እላለሁ፡፡ ጠንክሮ በመሥራት ጥቁር ወይም ሴት ሳይንቲስት መሆን አይችሉም፣ ጥሩ ማናጀር መሆን አይችሉም፣ መሪ መሆን አይችሉም የሚሉትን ማሳፈር ይቻላል” ትላለች፡፡ ይሄንንም በተግባር አሳይታለች፡፡

በአንድ ወቅት አውሮፓዊ ከሆነው ባለቤቷ’ጋ ስትኖር ያጋጠማትን ታስታውሳለች፡፡ “አዲስ የተቀጠረው የግቢያችን ጥበቃ ማታ በር አንኳኩቶ ስከፍትለት ‹ባለቤቷን ማናገር› እፈልጋለሁ ብሎኛል፡፡ እኔን ጥቁር ስለሆንኩ እንደ ባለቤት ሊቆጥረኝ አልፈለገም ነበር፡፡ አንዳንዴ ደግሞ በተሰጠኝ ኃላፊነት ተቀምጬ ባለጉዳዮች መጥተው ወንድ ኃላፊ ማናገር ሲፈልጉ ታዝቢያለሁ፡፡” በማለት ሰዎች በዘርና በፆታ መድሎና መገለል እደሚያደርሱና ይሄንንም ተጋፍጦ ማለፍ ወሳኝ እንደሆነ ታስረዳለች፡፡ “በዓለም ላይ ብዙ መልካም ሰዎች እንዳሉ መረዳት ወሳኝ ነው” የምትለው ዶ/ር ሰገነት “እኔ ባለፍኩበት ጎዳና በመላው ዓለም ብዙ መልካም ሰዎች ስላገዙኝ ጭምር ነው እዚህ የደረስኩት” በማለት ውለታቸውን ታስታውሳለች፡፡ “እዚህ ደረጃ እንድደርስ ያስተማሩኝ ቤተሰቦቼ ብቻ ሳይሆኑ መላው ያካባቢዬ ማኅበረሰብ እንደልጆቹ ይንከባከበኝ ስለነበር፣ አገሬም ትምህርት በነጻ የሰጠችኝ ስለሆነ፣ ባጠቃላይ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ያስተማሩኝ መምህራኖቼ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገውልኛል፡፡ ላከብራቸውና ላመሰግናቸው ይገባል” ትላለች፡፡

“አንድን ችግር የሚፈታ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤት ሲገኝ የሚሰማ ስሜት እጅግ የተለየ ነው” የምትለው ዶ/ር ሰገነት “ስሜቱን ለመግለጽ ከባድ፣ ሲሠሩት እንቅልፍ የሚነሳ፣ በትልቅ ደስታና ሐሴት ውስጥ የሚከት ነገር ነው” ትላለች፡፡ “አንዳንዴ ላብራቶሪ ውስጥ ማደርም አለ፡፡ ይሄም አስደሳች ነገር ነው፡፡”

## በዘርፉ ያበረከቱትና ያገኙት ሽልማት

ዶ/ር ሰገነት ቀለሙ በአሁኑ ጊዜ መቀመጫውን ናይሮቢ ኬኒያ ያደረገው ‹ኢንተርናሽናል ሴንተር ኦብ ኢንሴክት ፊዚኦሎጂ ኤንድ ኢኮሎጂ› የመጀመሪያዋ ሴት

> አዲስ የተቀጠረው የግቢያችን ጥበቃ ማታ በር አንኳኩቶ ስከፍትለት ‹ባለቤቷን ማናገር› እፈልጋለሁ ብሎኛል። እኔን ጥቁር ስለሆንኩ እንደ ባለቤት ሊቆጥረኝ አልፈለገም ነበር። አንዳንዴ ደግሞ በተሰጠኝ ኃላፊነት ተቀምጬ ባለጉዳዮች መጥተው ወንድ ኃላፊ ማናገር ሲፈልጉ ታዝቢያለሁ ”

## የሳይንቲስትነት ሕይወት

‹ለትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠትና መጠንከር እንዳለብኝ፣ ይሄም ከድህነት ማምለጫ ዋናው መንገድ እንደሆነ የተረዳሁት በልጅነቴ ነው› የምትለው ዶ/ር ሰገነት ‹ከልጅነቴ ጀምሮ በሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶች ጎበዝ ነበርኩ› ትላለች፡፡ “ሁልጊዜ ግን ሰብሎች አንድ ቀን በክፉ ተባዩች የሚያልቁ ይመስለኝ ነበር፡፡ ይሄም ሳይሆን አይቀርም ወደ እርሻ ሳይንስ እንድሳብ ያደረገኝ” ትላለች፡፡ “ለእርሻ ቅርብ ስለሆንኩ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችንም እረዳ ስለነበር፣ ለነዚህ ችግሮች መፍትሔ መፈለግ እንዳለብኝ ይሰማኝ ነበር፡፡ ሳይንስ ዘርፈ ብዙ የሆነውን የሰው ልጅ ችግር ለመቅረፍ ቁልፍ መፍትሔ እንዳለው አምናለሁ፡፡ በልጅነቴ ሰዎች ፔኒስሊን ስለሚባለው መድኃኒት ፈዋሽነት ሲያወሩ ስሰማ በጣም እደነቅ ነበር፡፡ ይህ መድኃኒት እስካሁን ከተሠሩ ፀረ-ባክቴሪያ መድኃኒቶች አቻ የለውም፡፡ በነዚህና መሰል የሳይንስ ግኝቶች ውስጤ ይመሰጥና ይገረም ስለነበር በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ለማኅበረሰቡና ለሰው ልጆች አንዳች ውጤት ያለው ነገር መሥራት ምኞቴ ነበር” ትላለች፡፡

እስካሁን ዐሥራሁለት የሚደርሱ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችን ለዓለም አበርክታለች፡፡

ዳይሬክተር ጀነራል ናቸው፡፡ ከዚያ በፊት ከ1992 እስከ 2007 እንደ ጎርጎሳውያን አቆጣጠር ካሊፎርኒያ በሚገኘው ‹ኢንተርናሽናል ሴንተር ፎር ትሮፒካል አግሪካልቸር› ውስጥ በ‹ሲኒዬር› ሳይንቲስትነትና የ‹ክሮፕ ኤንድ አግሮ ኢኮ ሲስተም› ክፍል ማኔጀር በመሆን አገልግላለች፡፡

ከሀያ አምስት ዓመት ብርቱ ምርምር በኋላ ወደ አፍሪካ በመመለስ ‹የኢንተርናሽናል ላይቭስቶክ ሪሰርች ኢንስቲትዩት› ዳይሬክተር ሆና ስታገለግል፣ አሁን ያለችበትን የኃላፊነት ቦታ ከመያዟ በፊት የ‹አሊያንስ ፎር ኤ ግሪን ሪቮሎዩሽን ኢን አፍሪካ› ተቀዳሚ ዳይሬክተር በመሆን ለአንድ ዓመት አገልግላለች፡፡

በነዚህ ሁሉ ኃላፊነቶች ለዓለማችንና ለሰው ልጆች ታላላቅ አስተዋፅዖዎችን አበርክታለች፡፡ በተለይ አሁን ባለችበት የሥራ ኃላፊነት እያበረከተች ያለውን ስትናገር “ይህ ኃላፊነት አስፈላጊም፣ ከሠሩበት ውለታ ከፋይም ነው፡፡ ለእኔ በአፍሪካ፣ በሳይንስ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ትልቅ ዕድል ነው” ትላለች፡፡ ተቋሙ ከትልልቅ የዓለማችን ተቋማት ጋር ስለሚሠራ የዓለምን ተሞክሮና ጥሬ ሀብትም በመጠቀም በአፍሪካ በግብርና ለሚደረግ ምርምር ታላቅ ፋይዳ ያለው ሥራ እየሠራ እንዳለ ብዙዎች ይመሰክራሉ፡፡ ይህ ተቋም በዓለማችን ብቸኛው በነፍሳት /Insects/ ላይ የምርምር

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

ሥራ የሚሠራ ተቋም ነው:: እነዚህ ነፍሳት ለአካባቢ፣ ለእፅዋት፣ ለሰው ልጆች ባጠቃላይ ለዓለማችን አስጊም ጠቃሚም እንደሆኑ የሚናገሩት ባለሙያዎች በዚህ ላይ የሚደረግ ምርምር በተለይ ለግብርናው ዘርፍ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው ይላሉ:: በመሆኑም ተቋሙ በዘርፉ ያካሄደው ምርምርና ውጤቱ በዓለማችን ታላላቅ ሚዲያዎች በተፅዕኖ ፈጣሪነቱና በለውጥ አምጭነቱ ተወድሷል::

ዶ/ር ሰገነት እንደ ጎርጎሳውያን አቆጣጠር በ20014 የ‹L'Oréal-UNESCO for Women in Science Awards› ከዓለማችን ሴት ሳይንቲስቶች ከአምስቱ አንዷ በመሆን ተሸላሚ ሆናለች:: በተጨማሪም በዚሁ ዓመት ‹ፎርብስ አፍሪካ› መጽሔት ከ100 የአፍሪካ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴቶች አንዷ አድርጎ የመረጣት ሲሆን የቻይና መንግሥት የሚሰጠውን ለተከበሩ ሰዎች የሚሰጥ ሽልማትም ተቀብላለች:: የአፍሪካ ሳይንስ አካዳሚ 26ኛ መደበኛ ስብሰባውን በ19 ‹ኖቬምበር› 2015 ቬና፣ ኦስትሪያ ባካሄደበት ወቅት ዶ/ር ሰገነት ለሳይንስ ላበረከተችው አስተዋፅዖ የተቋሙ ‹ፌሎው› ተደርጋ ተመርጣለች::

በሜይ 2016 የቴላቪቭ ዩኒቨርሲቲ ለዶ/ር ሰገነት በአፍሪካ ሴት ፋና ወጊ ሳይንቲስት በመሆኗ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተስማሚ የሆነ የእህል ዘርን እንዲኖር በሚደረግ ምርምር ላበረከተችው አስተዋፅዖ፣ በአፍሪካ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ የምርምር ውጤት ስላበረከተች እንዲሁም የዩኔስኮ ሴት ሳይንቲስት ተሸላሚ በመሆኗ እና በሌሎችም ለሳይንስ እና ለሰው ልጆች ባበረከተቻቸው ሥራዎቿ ለክብር ዶክትሬትነት በማጨት ቢል ክሊንተን፣ አንጄላ መርኬል፣ ቶኒ ብሌር፣ ሽሞን ፔሬዝና ሌሎችም የዓለማችን ታዋቂ ሰዎች የተሸለሙትን የክብር ዶክትሬት ማዕረግ ሸልሟቸዋል:: "በነዚህ ሁሉ ሽልማቶችና ስኬቶች ጀርባ ኢትዮጵያ ስለምትጠራ በጣም ደስ ይለኛል:: በኢትዮጵያዊነቴም እኮራለሁ" ትላለች::

## ሳይንስ አብቦ እንዲስፋፋ

"አንድ አገር ከድህነት ለመውጣት ሳይንስ ትልቅ መሣሪያ ነው" የምትለው ዶ/ር ሰገነት "በአፍሪካና በአውሮፓ መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት የሠለጠነ ሰው ኃይልና ሳይንስና ቴክኖሎጂን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞና ፈጠራ ጨምሮ ለችግሮቻችን መፍቻነት አለመጠቀም ነው" ትላለች:: "ለሳይንስ ምርምርና ጥናት ትልቅ ትኩረት የሚሰጡ አገራት ብዙውን ችግሮቻቸውን በራሳቸው ለመፍታት ችለዋል:: በሳይንስ ዘርፍ ውጤት ለማምጣት ብርቱ ጥረት፣ ልፋትና ጊዜ ይፈልጋል" የምትለው ዶ/ር ሰገነት "ውጤቱ ግን አስደሳችና ለግላችን ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጆች ስለሆነ ጥቅሙ እጥፍ ድርብ ነው" ትላለች::

"አቅምን ማጎልበት፣ ለሳይንስና ለምርምር ተገቢውን ትኩረት መስጠት፣ ሳይንስ እንዲያብብና ፍሬ እንዲያፈራ ወሳኝ ነው" የምትለው ዶ/ር ሰገነት አቅምን ማጎልበት ሲባል ግን ጥራት ላይ ማተኮር ዋናው ጉዳይ መሆን እንዳለበት አፅንዖት ሰጥታ ትናገራለች:: "ለሳይንስ ብዙ መዋዕለ ንዋያቸውን የሚፈሱ አገሮች በዓለማችን ላይ በመሪነት የተቀመጡ ናቸው" በማለት ለሳይንስ መሰጠት ስላለበት ትኩረት ታስረዳለች:: እዚህ ላይ ሴቶች መረሳት እደሌለባቸው የምትናገረው ዶ/ር ሰገነት ብዙ ጊዜ ሳይንስን የወንድ ተግባር አድርጎ የመውሰድ የተሳሳተ ዝንባሌ በመኖሩ ሴቶች ብቁ ሳይንቲስት መሆን እንደሚችሉና ትኩረት ሊሰጣቸው እነደሚገባ አበክራ ትናገራለች::

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ተማሪዎች ዘንድ የእንግሊዘኛ ችሎታ ማነስ እንደሚስተዋል የምትናገረው ዶ/ር ሰገነት ‹እንግሊዘኛ የዓለም የመግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል› ትላለች:: ‹የቱንም ያህል ችሎታ ያላቸው ልጆች ቢኖሩም በእንግሊዘኛ የመግባባትና የመጻፍ ችግር ካለ ካሰቡት ለመድረስ ስለሚቸገሩ በሁሉም ት/ቤቶች ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል› ትላለች::

*መብራቱ በላቸውን በኢሜይል አድራሻው mebre2001@gmail.com ሊያገኙት ይችላሉ።*





ሲቪክ ማኅበራት እና
የዴሞክራሲ ሽግግር

የሕዝብ ጥያቄን ማሰር
ይቻላል?

ዶ/ር ሰገነት
የስኬት ተምሳሌት




ከየ15 ቀኑ የሚታተም


# ውይይት

#Weyeyet

የምክንያታዊነት ድምፅ


ውይይት 1ኛ ዓመት|ቁጥር 7|ሐምሌ 2008|ዋጋ 13ብር




## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምን እያስመረቁ ነው?

መምህራን፤ "ተማሪዎቹ ብቁ አይደሉም"
ተማሪዎች፤ "መምህራኑ ብቁ አይደሉም"